# በየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤት

# የ6ኛ ክፍል ሂሳብ ሞዴል ፈተና

# ጥር,2016 ዓ.ም

የጥያቄ ብዛት: 30 የተፈቀደው ሰዓት: - 1 ሰዓት

**አጠቃላይ ትዕዛዝ**

ይህ ሂሳብ ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ 30 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል። በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል። መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት።

ፈተናውን ሰረቶ ለመጨርስ የተፈቀደው ሰአት 1 ሰአት ነው። ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለብን። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን። መኮረጅ ወይም በፈተና ሰዓት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል።

ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት።

ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !



LIVEWORKSHEETS

1. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ለ2 ተካፋይ የሆነ ሙሉ ቁጥር ለ4 ተካፋይ ነው

ለ. ለ10 ተካፋይ የሆነ ሙሉ ቁጥር ለ5 ተካፋይ ነው

ሐ. ለ6 ተካፋይ የሆነ ሙሉ ቁጥር ለ3 ተካፋይ ነው

መ. ለ8 ተካፋይ የሆነ ሙሉ ቁጥር ለ4 ተካፋይ ነው

2. ለሙሉ ቁጥሮች በሙሉ አካፋይ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. 2 ለ. 0 ሐ. 1 መ. 5

3. በሙሉ ቁጥር 431መ በ6 ተካፋይ እንዲሆን በመ ቦታ ላይ ሊገባ የሚችል ባለ አንድ ሙሉ ቁጥር ስንት ነው?

ሀ. 1 ለ. 4 ሐ. 7 መ. 8

4. የ287 አካፋይ የሆነው የሆነው ሙሉ ቁጥር የቱ ነው?

ሀ. 2 ለ. 3 ሐ. 7 መ. 8

5. ከሚከተሉት ውስጥ ብቸኛ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. 1001 ለ. 171 ሐ. 143 መ. 107

6. 780 በብቸኛ ትንትን ሲገለፅ የቱ ነው?

ሀ. $2^3 \times 3 \times 5 \times 13$ ለ. $2^2 \times 3^2 \times 5 \times 13$ ሐ. $2^2 \times 3 \times 5 \times 13$ መ. $2^2 \times 3 \times 5 \times 13^2$

7. የ15 ፣45፣135 ት.ጋ.አ ስንት ነው?

ሀ. 45 ለ. 60 ሐ. 15 መ. 1

8. ሸ=$2^3 \times 3 \times 5$፣ ቀ=$2 \times 3^2$ ከሆነ የሸ እና የቀ ት.ጋ.ብ ስንት ነው?

ሀ.2 ለ. 40 ሐ. 180 መ. 360

9. የሁለት ሙሉ ቁጥሮች ብዜት 300 ነው።የሁለቱ ት.ጋ.ብ 60 ቢሆን ት.ጋ.አ ስንት ነው?

ሀ. 25 ለ. 5 ሐ. 10 መ. 8

10. $\frac{90}{112}$ ወደ ዝቅተኛ ሂሳባዊ ቃል ሲለወጥ የቱ ነው?

ሀ. $\frac{45}{56}$ ለ. $\frac{3}{8}$ ሐ. $\frac{5}{8}$ መ. $\frac{28}{25}$

11. $3\frac{1}{5}$ ወደ አስርዮሽ ሲለወጥ የቱ ነው?

ሀ. 0.2 ለ. 3.5 ሐ. 0.5 መ. 3.2



LIVEWORKSHEETS

12. $\frac{23}{50}$ወደ መቶኛ (ፐርሰንት) ሲለወጥ የቱ ነው?

ሀ. 23% ለ. 46% ሐ. $\frac{23}{100}$ መ. $\frac{46}{3}$%

13. 1.25 ወደ ክፍልፋይ ሲለወጥ የቱ ነው?

ሀ. $\frac{5}{4}$ ለ. $\frac{3}{4}$ ሐ. $\frac{4}{5}$ መ. $\frac{7}{5}$

14. 0.025 ወደ መቶኛ (ፐርሰንት) ሲለወጥ የቱ ነው?

ሀ. 2.5% ለ. $\frac{25}{10}$% ሐ. $\frac{25}{100}$ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

15. $2\frac{1}{5}$% ወደ ክፍልፋይ ሲለወጥ የቱ ነው?

ሀ. $\frac{11}{100}$ ለ. $\frac{11}{10}$ ሐ. $\frac{11}{500}$ መ. $\frac{11}{5}$

16. 0.02% ወደ አስርዮሽ ቁጥር ሲለወጥ የቱ ነው?

ሀ. 0.02 ለ. 0.002 ሐ. 0.0002 መ. 0.2

17. ከ$\frac{2}{5}$----45% በማወዳደር በባዶ ቦታ ላይ ሊገባ የሚችል ምልክት የቱ ነው?

ሀ. > ለ. < ሐ. = መ. ሁሉም መልስ ናቸው

18. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. $\frac{7}{5}$ = 140% ለ. 0.2 = $\frac{1}{5}$ ሐ. 0.5 = 50% መ. $\frac{2}{25}$ = 0.4

19. ከሚከተሉት ውስጥ ከትንሹ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተል የተቀመጠው የቱ ነው?

ሀ. $\frac{3}{5}$፣$\frac{1}{4}$፣$\frac{2}{3}$፣$\frac{1}{4}$ ለ. $\frac{2}{3}$፣$\frac{3}{5}$፣$\frac{1}{2}$፣$\frac{1}{4}$ ሐ. $\frac{1}{4}$፣$\frac{1}{2}$፣$\frac{2}{3}$፣$\frac{3}{5}$ መ. $\frac{1}{4}$፣$\frac{1}{2}$፣$\frac{3}{5}$፣$\frac{2}{3}$

20. አንድ ተማሪ በሂሳብ ትምህርት ፈተና ከ30 18 ቢያመጣ በመቶኛ ስንት ይሆናል?

ሀ. 50% ለ. 60% ሐ. 30% መ. 20%

21. አልማዝ ለአንደኛዋ $2\frac{1}{4}$ኪ.ግ ሙዝ፣ለሁተኛዋ ደግሞ 3.75 ሙዝ ሰጠች። አልማዝ ለሁለቱም ስንት ኪ.ግ ሙዝ ሰጠች?

ሀ. 6.25 ለ. $\frac{25}{4}$ ሐ. 6 መ. $\frac{4}{25}$



LIVEWORKSHEETS

22. $6\frac{2}{5}$ + 0.225=---------

ሀ. $6\frac{5}{8}$ ለ. 6.525 ሐ. $\frac{51}{8}$ መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው

23. 2.25 - $\frac{1}{25}$ =-------

ሀ. $3\frac{21}{100}$ ለ. $\frac{221}{10}$ ሐ. 2.21 መ. ሁሉም መልስ ናቸው

24. ወ/ሮ አየለች 6ኪ.ግ ሸንኩርት ገዛች፡፡ ወ/ሮ አየለች ከገዛችው ውስጥ $3\frac{1}{8}$ ኪ.ግ ተጠቀመች፡፡ ወ/ሮ አየለች ስንት ኪ.ግ ሸንኩርት ይቀራታል?

ሀ. $\frac{23}{8}$ ለ. $2\frac{7}{8}$ ሐ. 2.875 መ. ሁሉም መልስ ናቸው

25. $6\frac{1}{4} \times 0.5$ =---------

ሀ. $\frac{8}{25}$ ለ. $3\frac{1}{8}$ ሐ. $\frac{25}{8}$ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

26. የአንድ ደብተር ዋጋ $10\frac{3}{5}$ ነው፡፡የ15 ደብተሮች ዋጋ ስንት ነው?

ሀ. 259 ለ. 159 ሐ. 359 መ. 59

27. 0.25 ÷ $1\frac{2}{5}$ =--------

ሀ. $\frac{5}{28}$ ለ. 0.28 ሐ. $\frac{28}{5}$ መ. $5\frac{3}{5}$

28. አንድ ሯጭ 15 ኪ.ሜ ለመሮጥ 0.5 ሰዓት ፈጀበት፡፡ፍጥነቱ በሰዓት ስንት ኪ.ሜ ነው?

ሀ. 40 ለ. 30 ሐ. 10 መ. 20

29. ተማሪ አልማዝ ከ30 ጥያቄ ውስጥ 80% ብትመልስ ተማሪ አልማዝ የመለሰችው ስንት ማርክ ነው?

ሀ. 10 ለ. 8 ሐ. 6 መ. 24

30. 986.201 በዚህ ቁጥር ውስጥ 1 የስንት ቤት ዋጋ አላት

ሀ. የመቶ ቤት ለ. የመቶኛ ቤት ሐ. የሺ ቤት መ. የሺኛ ቤት



LIVEWORKSHEETS